# <u>ምነዋ ቅጥፈቱ ቢያበቃ?</u>

ከበደ አሊ

በኢትዮጵያ ምድር ገና መራራ እውነቱ ተነግሮ ሳያበቃ ወደ ቅጥፈትና ውሸት ማምራት ምን ይባላል? ግፍ ሰርተው፤ የንፁህን ደም አፍሰው ዛሬ በየድርጅቱ ተደብቀው ያሉ ወንጀለኞች ያመለጡ መስሏቸው ቢቀጥፉ ባንደግፍም በገባንወ ይም መነሻ መድረሻቸው በተሰባን--በገባን-- ነበር። ግን ከሕዝብ ወገን ነን ብለው ነጭ ውሸት የሚዋሹት ግን ጉዶች ቢባሉ ሲያንስ እንጂ የሚበዛ አይደለም፡

በቅርቡ ልጀምርና የታወቀው ፊልም ሰሪ ኃይሌ ገሪማ በሰራው አዲስ ፊልም ስለ ቀይ ሽብር ሀቅ ያልሆኑ አቀራረቦችን ያዘለ ነው። በአንድ ቦታ ለምሳሌ አንዲት ሴት የሆነ ሰውን ሞት ተፈርዶብሀል ተለውና ብድግ ብላስትሄድ ሌላ ወጣት ከጎን በጥይት ይመታዋል። አቶ ኃይሌ ሊያሳይ የሚሞክረው ኢሕአፓ በዘፈቀደ የተቃወመውን ሁሉ ገዳይ ነበር፤ የሚገድላቸውንም በቅድሚያ ልትገ ደሉ ብሎ ይነግር ነበር ወዘተ በሚል ያው ኢሕአፓም የቀይ ሽብር አራማጆች ያክል ግድያ ያካሂድ ነበር የሚል አሉታዊ መልዕክት ለማስተላለፍ ይሞክራል። የካናዳ ሴት ፅፋለት ግን መፅሀፍ ፃፍኩ ያለው ነጋ መዝለቂያም ኢሕአፓ ከአየር ይመጣና ተመልምለሃል ሲል እምቢ ካልክ ወዲያው በሽጉጥ ይገድልሀል ብሎ ቀጥፎ ነበር። ይህ ሁሉ ቅጥፈት የማያውቀውን ባዕድ ያደናግር እንደሁ እንጂ የነበረውን ለሚያውቀው ሀሰትነቱ አጠራጣሪ አይደለም። አቶ ኃይሌ ገሪማ ሚቹን ዘሩ ኬህሻንን አነጋገሩ ቢባልም ስለ ቀይ ሽብሩ የሚመለከታቸውን ወይም የሚያውቁትን በስፋት አላወያዩም። መረጃቸው ደካማና የተሳሳተ ነው። በመሆኑም ስለ ቀይ ሽብሩም ሆነ ኢሕአፓ ያቀረቡት ሀቅ አይደለም። ምነው ታዲያ የቅጥፈቱንና ስም ማጥፋቱን መንገድ መረጡ? በመጀመሪያ ፊልማቸውም ውስጥ የጎንደር ነዋሪዎች በአማርኛ ኢሕአፓ ሲሉ በእንግሊዝኛ ሲተረጉሙ ግን በደፈናው “ ተቃዋሚ” ብለው ማለፋቸውም ትዝ ይለኛል።

በአቶ ኃይሌ ፊልም ላይ በዝርዝር ወደፊት እመለስበታለሁ። ካለፈው ፊልማቸ ውም ኢሕአፓን እንደሚጠሉ መገንዘብ ችለናል። ፊልም ሰሪ እንደ ታሪክ ፀሀፊ ሚዛናዊ እንዲሆን ተስፋ ነበረን። ግን አልሆነም። ደራሲ በተለይም እንደ ነጋ መዝለቂያ የህይወት ታሪኬ  ብሎ የሚፅፍ/ ወይም የሚያፅፍ/ ሰው ቢያንስ አይዋሽም ብለን ብንገምት ልንወቀስ ባልቻለ ነበር። ነጋ ግን በፀሀፊዋ በኩል አድርጎ ዋሽቷል። ያልፃፈውን ፃፍኩ ብሎ ከመቅለሉ ባሻገር በታገለ ድርጅት ላይ አሳፋሪ ውሽትን አውርዶ ራሱን ይበልጥ አዋርዷል።

ምነዋ ሀቁ ተነግሮ ባላለቀበት ሀገር መዋሸቱ አስፈለገ ?